"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ፤ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ፣ በልቤም ትሁት ነኝ፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ፣ ሸክሜም ቀሊል ነው።" ማቴ 11፥28-30
(See below for English translation)

**ተልዕኮ**

ሻሎም የኢትዮጵያውያን ወንጌላዊት ሉቴራን ቤተክርስቲያን ተልዕኮ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቁ ተልዕኮን መታዘዝ፤ ይህም የምስራቹን ወንጌል ለአለም ሁሉ መስበክ፤ ማስተማር፤ ጌታ ያዘዘውን ሁሉ አማኞች እንዲጠብቁ ማበረታታት፤ ተልዕኮአቸውን ለመወጣት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ደቀመዛሙርት ሆነው እነርሱ በተራቸው ሌሎችን በክርስቶስ የፍቅር ወንጌል በመድረስ ደቀመዛሙርት እንዲያፈሩ ማዘጋጀት፤ ይህም በቃልና በኑሮአቸው የሚገለጥ አገልግሎት እንዲሆን መርዳት (ማቴ 28፥18-20፤ 2ጢሞ 2፥1-2፤ ሐዋ 1፥8)። ቤተክርስቲያናችን ለታላቁ ተልዕኮ ምላሽ በመስጠት የሰውን ሁለንተና (መንፈሱን፣ ነፍሱንና አካሉን) ማገልገል ተግባሯ ይሆናል:: በመላው አለም፣ መላውን ሰው፣ በመላው ወንጌል በማገልገል ለተልዕኮው ምላሽ መስጠት ይሆናል:: የቅዱሳት ሚስጥራትን ጠቀሜታ ለምዕመናን ማስተማርና ማገልገል የቤተክርስቲያናችን ቀዳሚ ተግባሯ ነው።

**ዓላማ**

የቤተክርስቲያናችን ዓላማ ምዕመናኑ እንደ እግዚአብሔር ቤተሰብ በአንድ ልብና በአንድ ሃሳብ በመሆን እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ማወደስና ለህያው እግዚአብሔር (ለአብ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ፡ አንድ አምላክ) እርሱ ስለሠራው ሥራ፣ በመሥራት ላይ ስላለው ነገር፣ ወደፊት ስለሚሰራውም ጭምር የተገባውን አክብሮትና ምስጋና መስጠት እንዲችሉ ምዕመናኑ ማዘጋጀት ነው።

ሁላችንም በአንድ ልብ ሆነን ቃሉን ለመማር ራሳችንን መስጠት፤ እንዲሁም በጸጋው ጉልበት የተማርነውን በመኖር በቃላችንና በኑሮአችን ምስክር በመሆን የአካባቢውን ህዝብ በመድረስ፣ የጠፉትን በክርስቶስ ወንጌል በመድረስ ወደ ህብረታችን እንዲመጡ መርዳት፤ ከክርስቶስና አካሉ ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ጋር ህብረት እንዲኖራቸው ማድረግ ዋንኛው ዓላማችን ነው። ሐዋ 4፥32-35፤ 1ዮሐ 1፥1-7

በቤተክርስቲያኒቱ አባሎች ህይወት ውስጥ በወንጌል ትምህርት መልካም ተጽእኖን በመፍጠር በውስጣቸው እግዚአብሔር ያስቀመጠው ጸጋ ወጥቶ ህብረተሰባቸውን በክርስቶስ ወንጌል በመድረስ ብቃት ያለውን አገልግሎት እንዲያበረክቱ መርዳት ትኩረታችን ነው።

**ጠቀሜታ (Value)**

ለጌታ የተሰጡ ግለሰቦች፣ በክርስቶስ የታመኑ፣ ለሌላው የሚጠነቀቁ፣ በጌታ የሚታመን አመራር፣ በትክክለኛው የወንጌል ትምህርት ወይም ዶክትሪን ላይ ጸንቶ መቆም፤ እውነተኛውን ትምህርት ወይም በክርስቶስ ያለውን እምነት መከላከል መቻል፤ እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠውን ጸጋ የክርስቶስን አካል ለማነጽ በስራ ላይ ማዋል፤ እንደ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት መታወቂያችንን "የእግዚአብሔር ፍቅር" ማድረግ:: የህብረትን ኑሮ ማሳደግ ወይም ማበረታታት፤ ትጋት የሚታይበት የጸሎት ህይወት እና በቃል እውቀት ለማደግ ጥረት ማድረግ፤ ወርቃማውን ትዕዛዝ በኑሮ ሁሉ መተግበር (ማቴ 7፥12)፤ እግዚአብሔር አምላክን በፍጹም ልብ፣ በፍጹም ነፍስ፣ እና በፍጹም ሃይል መውደድ (ዘዳ 6፥4-9)፤ እግዚአብሔርን መፍራትና መታዘዝ ምንጊዜም አጥብቀን የምንይዘውና ከልባችን የማይጠፋ ጉዳይ ነው::